# ትንቢተ ፡ ሚልክያስ ።

(ክለሳ.1.20020507)

ትንቢተ ፡ ሚልክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ።

## ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ በሚልክያስ ፡ እጅ ፡ ለእስራኤል ፡ የኾነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሸክም ፡ ይህ ፡ ነው ።

2 ፤ ወድጃችኋለኹ ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ እናንተ ፡ ግን ፦ በምን ፡ ወደድኸን ፧ ብላችኋል ። ዔሳው ፡ የያዕቆብ ፡ ወንድም ፡ አልነበረምን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፤ ያዕቆብንም ፡ ወደድኹ ፥ ዔሳውንም ፡ ጠላኹ ፤

3 ፤ ተራራዎቹንም ፡ በረሓ ፡ አደረግኋቸው ፥ ርስቱንም ፡ ለምድረ ፡ በዳ ፡ ቀበሮዎች ፡ አሳልፌ ፡ ሰጠኋቸው ።

4 ፤ ኤዶምያስ ፦ እኛ ፡ ፈርሰናል ፥ ነገር ፡ ግን ፥ የፈረሰውን ፡ መልሰን ፡ እንሠራለን ፡ ቢል ፥ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦ እነርሱ ፡ ይሠራሉ ፥ እኔ ፡ ግን ፡ አፈርሳለኹ ፤ በሰዎችም ፡ ዘንድ ፦ የበደል ፡ ዳርቻና ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዘለዓለም ፡ የተቈጣው ፡ ሕዝብ ፡ ይባላል ።

5 ፤ ዐይኖቻችኹም ፡ ያያሉ ፥ እናንተም ፦ እግዚአብሔር ፡ ከእስራኤል ፡ ዳርቻ ፡ ወዲያ ፡ ታላቅ ፡ ይኹን ፡ ትላላችኹ ።

6 ፤ እናንተ ፡ ስሜን ፡ የምታቃልሉ ፡ ካህናት ፡ ሆይ ፥ ልጅ ፡ አባቱን ፥ ባሪያም ፡ ጌታውን ፡ ያከብራል ፤ እኔስ ፡ አባት ፡ ከኾንኹ ፡ ክብሬ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ጌታስ ፡ ከኾንኹ ፡ መፈራቴ ፡ ወዴት ፡ አለ ፧ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። እናንተም ፦ ስምኽን ፡ ያቃለልን ፡ በምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኋል ።

7 ፤ በመሠዊያዬ ፡ ላይ ፡ ርኩስ ፡ እንጀራ ፡ ታቀርባላችኹ ። እናንተም ፦ ያረከስንኽ ፡ በምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኋል ። የእግዚአብሔር ፡ ገበታ ፡ የተነቀፈ ፡ ነው ፡ በማለታችኹ ፡ ነው ።

8 ፤ ዕውር ፡ መሥዋዕትንም ፡ ስታቀርቡ ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ አይደለምን ፧ ዐንካሳውንና ፡ የታመመውን ፡ ስታቀርቡ ፡ ይህ ፡ ክፉ ፡ አይደለምን ፧ ያንን ፡ ለአለቃኽ ፡ አቅርብ ፤ በእውኑ ፡ ባንተ ፡ ደስ ፡ ይለዋልን ፧ ወይስ ፡ ፊትኽን ፡ ይቀበላልን ፧ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

9 ፤ አኹንም ፡ ጸጋን ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለምኑ ፤ ይህ ፡ ከእጃችኹ ፡ የተሰጠ ፡ ሲኾን ፡ ከቶ ፡ ፊታችኹን ፡ ይቀበላልን ፧ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

10 ፤ በመሠዊያዬ ፡ ላይ ፡ እሳትን ፡ በከንቱ ፡ እንዳታቃጥሉ ፡ ከእናንተ ፡ ዘንድ ፡ ደጅ ፡ የሚዘጋ ፡ ሰው ፡ ምነው ፡ በተገኘ! በእናንተ ፡ ደስ ፡ አይለኝም ፥ ቍርባንንም ፡ ከእጃችኹ ፡ አልቀበልም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

11 ፤ ከፀሓይ ፡ መውጫ ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ መግቢያዋ ፡ ድረስ ፡ ስሜ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ይኾናልና ፤ በየስፍራውም ፡ ለስሜ ፡ ዕጣን ፡ ያጥናሉ ፥ ንጹሕም ፡ ቍርባን ፡ ያቀርባሉ ፤ ስሜ ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ይኾናልና ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

12 ፤ እናንተ ፡ ግን ፦ የእግዚአብሔር ፡ ገበታ ፡ ርኩስ ፡ ነው ፤ ፍሬውና ፡ መብሉም ፡ የተናቀ ፡ ነው ፡ በማለታችኹ ፡ አስነቀፋችኹት ።

13 ፤ እናንተ ፦ እንሆ ፥ ይህ ፡ ድካም ፡ ነው ፡ ብላችኹ ፡ ጢቅ ፡ አላችኹበት ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ በቅሚያ ፡ የያዛችኹትንም ፡ ዐንካሳውንም ፡ የታመመውንም ፡ አቅርባችኋል ፤ እንዲሁ ፡ ቍርባንን ፡ ታመጣላችኹ ፤ በእውኑ ፡ ከእጃችኹ ፡ ይህን ፡ ልቀበለውን ፧ ይላል ፡ እግዚአብሔር ።

14 ፤ እኔ ፡ ታላቅ ፡ ንጉሥ ፡ ነኝና ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፥ ስሜም ፡ በአሕዛብ ፡ ዘንድ ፡ የተፈራ ፡ ነውና ፥ በመንጋው ፡ ውስጥ ፡ ተባት ፡ እያለው ፡ ለጌታ ፡ ተስሎ ፡ ነውረኛውን ፡ የሚሠዋ ፡ ሸንጋይ ፡ ሰው ፡ ርጉም ፡ ይኹን ።

ትንቢተ ፡ ሚልክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ 2 ።

1 ፤ አኹንም ፡ እናንተ ፡ ካህናት ፡ ሆይ ፥ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ለእናንተ ፡ ነው ።

2 ፤ ለስሜ ፡ ክብር ፡ ትሰጡ ፡ ዘንድ ፡ ባትሰሙ ፥ በልባችኹም ፡ ባታደርጉት ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡
እግዚአብሔር ፥ ርግማን ፡ እሰድባችኋለኹ ፥ በረከታችኹንም ፡ እረግማታለኹ ፤ አኹንም ፡ በልባችኹ ፡
አላደረጋችኹትምና ፡ እኔ ፡ ረግሜያታለኹ ።

3 ፤ እንሆ ፥ ክንዳችኹን ፡ እገሥጻለኹ ፥ የመሥዋዕታችኹንም ፡ ፋንድያ ፡ በፊታችኹ ፡ ላይ ፡ እበትናለኹ ፤ ከርሱም ፡
ጋራ ፡ በአንድነት ፡ ትወሰዳላችኹ ።

4 ፤ ቃል ፡ ኪዳኔ ፡ ከሌዊ ፡ ጋራ ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ትእዛዝ ፡ እንደ ፡ ሰደድኹላችኹ ፡ ታውቃላችኹ ፥ ይላል ፡
የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

5 ፤ ቃል ፡ ኪዳኔ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የሕይወትና ፡ የሰላም ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ነበረ ፤ ይፈራ ፡ ዘንድም ፡ እነርሱን ፡
ሰጠኹት ፤ ርሱም ፡ ፈራኝ ፥ ከስሜም ፡ የተነሣ ፡ ደነገጠ ።

6 ፤ የእውነት ፡ ሕግ ፡ በአፉ ፡ ውስጥ ፡ ነበረች ፥ በከንፈሩም ፡ ውስጥ ፡ በደል ፡ አልተገኘበትም ፤ ከእኔም ፡ ጋራ ፡ በሰላምና ፡
በቅንነት ፡ ኼደ ፥ ብዙ ፡ ሰዎችንም ፡ ከኀጢአት ፡ መለሰ ።

7 ፤ ካህኑ ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልእክተኛ ፡ ነውና ፥ ከንፈሮቹ ፡ ዕውቀትን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡
ይገ̇ባ̇ቸዋል ፥ ሰዎችም ፡ ሕግን ፡ ከአፉ ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፡ ይገ̇ባ̇ቸዋል ።

8 ፤ እናንተ ፡ ግን ፡ ከመንገዱ ፡ ፈቀቅ ፡ ብላችኋል ፤ በሕግም ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ አሰናክላችኋል ፤ የሌዊንም ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ አስነውራችኋል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

9 ፤ ስለዚህ ፥ መንገዴን ፡ እንዳልጠበቃችኹ ፥ በሕግም ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ እንዳዳላችኹ ፡ መጠን ፥ እኔ ፡ ደግሞ ፡ በሕዝብ ፡
ኹሉ ፡ ፊት ፡ የተናቃችኹና ፡ የተዋረዳችኹ ፡ አድርጌያችኋለኹ ።

10 ፤ ለኹላችን ፡ አንድ ፡ አባት ፡ ያለን ፡ አይደለምን ፧ አንድ ፡ አምላክስ ፡ የፈጠረን ፡ አይደለምን ፧ የአባቶቻችንን ፡ ቃል ፡
ኪዳን ፡ ለማስነቀፍ ፡ እኛ ፡ እያንዳንዳችን ፡ ወንድማችንን ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አታለልን ፧

11 ፤ እግዚአብሔር ፡ የወደደውን ፡ መቅደስ ፡ ይሁዳ ፡ አርክሷልና ፥ የእንግዳውንም ፡ አምላክ ፡ ልጅ ፡ ሚስት ፡ አድርጎ ፡
አግብቷልና ፥ ይሁዳ ፡ አ̇ታ̇ሏል ፥ በእስራኤልና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ውስጥ ፡ ርኩሰት ፡ ተሠርቷል ።

12 ፤ ይህን ፡ ከሚያደርግ ፡ ሰው ፥ እግዚአብሔር ፡ የሚጠራውንና ፡ የሚመልሰውን ፡ ለሰራዊትም ፡ ጌታ ፡ ለእግዚአብሔር ፡
ቍርባን ፡ የሚያቀርበውን ፡ ከያዕቆብ ፡ ድንኳን ፡ ያጠፋል ።

13 ፤ ይህንም ፡ ደግሞ ፡ አድርጋችኋል ፤ እግዚአብሔር ፡ ቍርባኑን ፡ ዳግመኛ ፡ እንዳይመለከት ፥ ከእጃችኹም ፡ በደስታ ፡
እንዳይቀበለው ፡ መሠዊያውን ፡ በእንባና ፡ በልቅሶ ፡ በሐዘንም ፡ ትከድናላችኹ ።

14 ፤ እናንተም ፦ ስለ ፡ ምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኋል ። ሚስትኽ ፡ ባልንጀራኽና ፡ የቃል ፡ ኪዳንኽ ፡ ሚስት ፡ ኾና ፡ ሳለች ፡
ርሷን ፡ አ̇ታ̇ለ̇ኻታልና ፥ እግዚአብሔር ፡ በአንተና ፡ በልጅነት ፡ ሚስትኽ ፡ መካከል ፡ ምስክር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፡ ነው ።

15 ፤ እግዚአብሔር ፡ የሕይወትን ፡ መንፈስ ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ጠብቆልን ፡ የለምን ፧ ርሱም ፡ የሚፈልገው ፡ ምንድር ፡
ነው ፧ ዘር ፡ አይደለምን ፧ ስለዚህ ፡ መንፈሳችኹን ፡ ጠብቁ ፥ ማንም ፡ የልጅነት ፡ ሚስቱን ፡ አያታል̇ ።

16 ፤ መፋታትን ፡ እጠላለኹ ፥ ይላል ፡ የእስራኤል ፡ አምላክ ፡ እግዚአብሔር ፥ ልብሱንም ፡ በግፍ ፡ ሥራ ፡ የሚከድነውን ፡
ሰው ፡ እጠላለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ስለዚህ ፥ እንዳታታልሉ ፡ መንፈሳችኹን ፡ ጠብቁ ።

17 ፤ እግዚአብሔርን ፡ በቃላችኹ ፡ አታክታችኋል ። እናንተም ፦ ያታከትነው ፡ በምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኋል ። ክፉን ፡
የሚያደርግ ፡ ኹሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ መልካም ፡ ነው ፥ ርሱም ፡ በእነርሱ ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፤ ወይስ ። የፍርድ ፡
አምላክ ፡ወዴት ፡ አለ ፧ በማለታችኹ ፡ ነው ።

________________ትንቢተ ፡ ሚልክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። ________________

ምዕራፍ ፡ 3 ።



www.ethiopianorthodox.org

1 ፤ እንሆ ፥ መልእክተኛዬን ፡ እልካለኹ ፥ መንገድንም ፡ በፊቴ ፡ ያስተካክላል ፤ እናንተም ፡ የምትፈልጉት ፡ ጌታ ፡ በድንገት ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ ይመጣል ፤ የምትወዱትም ፡ የቃል ፡ ኪዳን ፡ መልእክተኛ ፥ እንሆ ፥ ይመጣል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ርሱ ፡ እንደ ፡ አንጥረኛ ፡ እሳትና ፡ እንደ ፡ ዐጣቢ ፡ ሳሙና ፡ ነውና ፥ የሚመጣበትን ፡ ቀን ፡ መታገሥ ፡ የሚችል ፡ ማን ፡ ነው ፧ ርሱስ ፡ በተገለጠ ፡ ጊዜ ፡ የሚቆም ፡ ማን ፡ ነው ፧

3 ፤ ርሱም ፡ ብርን ፡ እንደሚያነጥርና ፡ እንደሚያጠራ ፡ ሰው ፡ ይቀመጣል ፥ የሌዊንም ፡ ልጆች ፡ ያጠራል ፥ እንደ ፡ ወርቅና ፡ እንደ ፡ ብርም ፡ ያነጥራቸዋል ፤ እነርሱም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በጽድቅ ፡ ቍርባንን ፡ የሚያቀርቡ ፡ ይኾናሉ ።

4 ፤ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ ዱሮው ፡ ዘመንና ፡ እንደ ፡ ቀደሙት ፡ ዓመታት ፡ በይሁዳና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቍርባን ፡ ደስ ፡ ይለዋል ።

5 ፤ ለፍርድ ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እቀርባለኹ ፤ በመተተኛዎችና ፡ በአመንዝራዎች ፥ በሐሰትም ፡ በሚምሉ ፥ የምንደኛውን ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ በሚከለክሉ ፥ መበለቲቱንና ፡ ድኻ ፡ አደጉን ፡ በሚያስጨንቁ ፥ የመጻተኛውንም ፡ ፍርድ ፡ በሚያጣምሙ ፥ እኔንም ፡ በማይፈሩ ፡ ላይ ፡ ፈጣን ፡ ምስክር ፡ እኾንባቸዋለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

6 ፤ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልለወጥም ፤ እናንተ ፡ የያዕቆብ ፡ ልጆች ፡ ሆይ ፥ ስለዚህ ፡ የጠፋችኹ ፡ አይደላችኹም ።

7 ፤ ከአባቶቻችኹ ፡ ዘመን ፡ ዠምር ፡ ከሥርዐቴ ፡ ፈቀቅ ፡ ብላችኋል ፥ ርሷንም ፡ አልጠበቃችኹም ፦ ወደ ፡ እኔ ፡ ተመለሱ ፥ እኔም ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ እመለሳለኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ። እናንተ ፡ ግን ፦ የምንመለሰው ፡ በምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኋል ።

8 ፤ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይሰርቃልን ፧ እናንተ ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ሰርቃችኋል ። እናንተም ፦ የሰረቅንኽ ፡ በምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኋል ። በዓሥራትና ፡ በበኵራት ፡ ነው ።

9 ፤ እናንተ ፥ ይህ ፡ ሕዝብ ፡ ኹሉ ፥ እኔን ፡ ሰርቃችኋልና ፥ በርግማን ፡ ርጉሞች ፡ ናችኹ ።

10 ፤ በቤቴ ፡ ውስጥ ፡ መብል ፡ እንዲኾን ፡ ዓሥራቱን ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ጐተራ ፡ አግቡ ፤ የሰማይንም ፡ መስኮት ፡ ባልከፍትላችኹ ፥ በረከትንም ፡ አትረፍርፌ ፡ ባላፈስላችኹ ፡ በዚህ ፡ ፈትኑኝ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

11 ፤ ስለ ፡ እናንተ ፡ ነቀዙን ፡ እገሥጻለኹ ፥ የምድራችኹንም ፡ ፍሬ ፡ አያጠፋም ፤ በዕርሻችኹም ፡ ያለው ፡ ወይን ፡ ፍሬውን ፡ አያረግፍም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

12 ፤ የተድላ ፡ ምድር ፡ ትኾናላችኹና ፡ አሕዛብ ፡ ኹሉ ፡ ብፁዓን ፡ ብለው ፡ ይጠሯችኋል ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

13 ፤ ቃላችኹ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ድፍረት ፡ ኾኗል ፥ ይላል ፡ እግዚአብሔር ። እናንተ ፡ ግን ፦ ባንተ ፡ ላይ ፡ ደፍረን ፡ የተናገርነው ፡ በምንድር ፡ ነው ፧ ብላችኋል ።

14 ፤ እናንተም ፦ እግዚአብሔርን ፡ ማገልገል ፡ ከንቱ ፡ ነው ፤ ትእዛዙንስ ፡ በመጠበቅ ፥ በሰራዊት ፡ ጌታ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ሐዘንተኛዎች ፡ ኾነን ፡ በመኼድ ፡ ምን ፡ ይረባናል ፧

15 ፤ አኹንም ፡ የሚታበዩትን ፡ ሰዎች ፡ ብፁዓን ፡ ብለን ፡ እንጠራቸዋለን ፤ ክፉንም ፡ የሚሠሩ ፡ ጸንተዋል ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ይፈታተናሉ ፥ ያመልጣሉም ፡ ብላችኋል ።

16 ፤ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈሩ ፡ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ተነጋገሩ ፤ እግዚአብሔርም ፡ አደመጠ ፥ ሰማም ፥ እግዚአብሔርንም ፡ ለሚፈሩ ፡ ስሙንም ፡ ለሚያስቡ ፡ የመታሰቢያ ፡ መጽሐፍ ፡ በፊቱ ፡ ተጻፈ ።

17 ፤ እኔ ፡ በምሠራበት ፡ ቀን ፡ እነርሱ ፡ የእኔ ፡ ገንዘብ ፡ ይኾናሉ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፤ ሰውም ፡ የሚያገለግለውን ፡ ልጁን ፡ እንደሚምር ፥ እንዲሁ ፡ እምራቸዋለኹ ።

18 ፤ ተመልሳችኹም ፡ በጻድቁና ፡ በኀጢአተኛው ፡ መካከል ፥ ለእግዚአብሔር ፡ በሚገዛውና ፡ በማይገዛው ፡ መካከል ፡ ትለያላችኹ ።

________________ትንቢተ ፡ ሚልክያስ ፥ ምዕራፍ ፡ 4 ። ________________



www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፡ 4 ።

1 ፤ እንሆ ፥ እንደ ፡ ምድጃ ፡ እሳት ፡ የሚነድ ፡ ቀን ፡ ይመጣል ፤ ትዕቢተኛዎችና ፡ ኀጢአትን ፡ የሚሠሩ ፡ ዅሉ ፡ ገለባ ፡
ይኾናሉ ፤ የሚመጣውም ፡ ቀን ፡ ያቃጥላቸዋል ፥ ሥርንና ፡ ቅርንጫፍንም ፡ አይተውላቸውም ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡
እግዚአብሔር ።

2 ፤ ነገር ፡ ግን ፥ ስሜን ፡ ለምትፈሩት ፡ ለእናንተ ፡ የጽድቅ ፡ ፀሓይ ፡ ትወጣላችኋለች ፥ ፈውስም ፡ በክንፎቿ ፡ ውስጥ ፡
ይኾናል ፤ እናንተም ፡ ትወጣላችኹ ፥ እንደ ፡ ሰባም ፡ እንቦሳ ፡ ትፈነጫላችኹ ።

3 ፤ በምሠራበት ፡ ቀን ፡ በደለኛዎች ፡ ከእግራችኹ ፡ ጫማ ፡ በታች ፡ ዐመድ ፡ ይኾናሉና ፡ እናንተ ፡
ትረግጧቸዋላችኹ ፥ ይላል ፡ የሰራዊት ፡ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ።

4 ፤ ለእስራኤል ፡ ዅሉ ፡ ሥርዐትንና ፡ ፍርድን ፡ አድርጌ ፡ በኰሬብ ፡ ያዘዝኹትን ፡ የባሪያዬን ፡ የሙሴን ፡ ሕግ ፡ ዐስቡ ።

5 ፤ እንሆ ፥ ታላቁና ፡ የሚያስፈራው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቀን ፡ ሳይመጣ ፡ ነቢዩን ፡ ኤልያስን ፡ እልክላችኋለኹ ።

6 ፤ መጥቼም ፡ ምድርን ፡ በርግማን ፡ እንዳልመታ ፡ ርሱ ፡ የአባቶችን ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ ልጆች ፥ የልጆችንም ፡ ልብ ፡ ወደ ፡
አባቶች ፡ ይመልሳል ፨



www.ethiopianorthodox.org